Amharic

Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission

simply your rights

# አድልዎ በዘር ጥላቻ

## Discrimination - Race

አንድ ሰው ባለው ባህሪ አስመልክቶ ያለአግባብ ወይም በመጥፎ ሁኔታ ከተስተናገደ አድልዎ ደረሰበት ይባላል። የአንድን ሰው ዘር አስመልክቶ አድልዎ መፍጠር በቪክቶሪያ ውስጥ ህገወጥነት ነው።

### ዘር ማለት ምንድነው?

ይህ የቀለም፥ ጭዋነት፥ የመጡበት አገር፥ የዘር ሀረግ፥ የጎሳ ወይም ከአንድ የሰው ዘር ባህሪ ጋር ማመሳሰል ይሆናል።

---

**ምሳሌዎች**

(አበበ መላኩ) በህንጻ ኩባንያ ስራ አመልክቶ ተቀባይነት አላገኘም። ለምን ስራውን እንዳላገኘ ለመጠየቅ ሲል ለኩባንያው ሲደውል፤ ለ (አበበ መላኩ) የተሰጠው መልስ፥ "ቀደም ሲል ከአንተ አገር ሰዎች የተቀጠሩ እንደነበሩ ነው። እናንተ በቀላሉ የእኛን የስራ ግብረገብነት ህጎችን በጋራ አትፈጽሙም። ስለዚህ ያንን ስሕተት መድገም አንፈልግም።"

### የዘር አድልዎ የሚደረገው የት ላይ ነው?

ህጉ ተግባራዊ የሚሆነው በአደባባይ ለሚደረጉ ጠባይ እንጂ በግል ለሚድርጉ ነገሮች አይደለም። ይህ ማለት በስራ አካባቢ፥ በመጠለያ፥ በክለቦች፥ በትምህርት፥ በእቃና አገልግሎት መስጫ፥ በስፖርት እና መሬት ሲሸጡና በሚያዛወሩበት ጊዜ የዘር ልዩነት መፍጠር ህገወጥ ያሰኛል

---

**ለምሳሌ:**

ደረጀ እና አስቴር ኢትዮጵያ ች ናቸው። በአካባቢያቸው ባለ የአጸደ ህጻናት ውስጥ ለልጃቸው (አቤል) ክፍት ቦታ ካለ ለመጠየቅ ስልክ በሚደውሉበት ጊዜ፥ እንደተነገራቸው "አዎ ብዙ ቦታ በክፍሉ ውስጥ እንዳለ ነው።" ነገር ግን አስቴር ልጁን (ቤልን) ይዛ ወደ አጸደ ህጻናቱ በምትሄድበት ጊዜ ስራ አስኪያጁ ለልጁ ወደሚሰማማው ቦታ ይዛው እንድትሄድ ነገራት።

### የማይመለከታቸው

በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ የሰው ዘርን በመለየት አድልዎ እንዲፈጠር ይሆናል። ለምሳሌ በዩክራኒያን በእድሜ ለገፉ የእንክብካቤ መስጫ ሆስቴል ውሰጥ ከዩክራኒያን ዝርያ ሌላ ሰው እንደማይፈቀድለት ሲሆን በሰልቲክ ክለብ ለሰልቲክ ዝርያ ላላው አባላት ብቻ ሲሆን በጃፓን በጎ አድራጎት ማህበር ውስጥ መስራት የሚችለው ለጃፓን ሰዎች ብቻ ይሆናል።

አስፈላጊ ከሆነ የድራማ ትርኢት፥ የስነ ጥበብ ስራ፥ የማዝናኛ ስራ፥ የፎቶግራፍ ወይም የሞዴል ስራ ለማካሄድ ሲባል አንድ ቀጣሪ ድርጅት ለተወሰኑ የሰው ዘር ስራ መስጠት ይችላል።

### እንዴት የቪክቶሪያ እኩልነት አስከባሪና የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ሊረዳ ይችላል?

ሰዎች በሚኖራቸው የአድልዎ ቅሬታ የጋራ ስምምነት ለማግኘት ሚስጢራዊ በሆነ፣ በነጻና ወገናዊነት በሌለው የመፍትሄ አገልግሎት እርዳታ እናቀርባለን። ቅሬታዎች በግለሰብ፣ በተወካይ ወይንም በድርጅቶች በኩል ሊቀርብ ይችላል። ለኮሚሽኑ ደውሎ በነጻ አስተርጓሚ ካስፈለግዎ እንዲቀርብልዎ መጠየቅ ነው።

**ለምክር መስመር (03) 9281 7100**
**በነጻ ለመደወል (በገጠር ሆኖ ለሚደውል) 1800 134 142**
**መስማትና መናገር ለማይችል/TTY: (03) 9281 7110**
**ኢ.ሜል: complaints@veohrc.vic.gov.au**

በጥያቄ ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎት ይቀርባል።

---

**የክህደት ቃል**: ይህ ለመረጃ አቅርቦት መመሪያ ብቻ ተብሎ የቀረበ ነው። የህጋዊ የሆነን ምክር አይተካም።
**የርስዎ ብቻነት**: በቪክቶሪያ ነዋሪዎች የብቻነት ህጎች ላይ በእኩልነት መብት አስከባሪ የ1995 ዓ.ም አንቀጽ ህግ መሰረት የVEO&HRC ይከተላል። የብቻነት ፖሊሲያችን በድረገጽ፤ www.humanrightscommission.vic.gov.au/privacy ላይ ይቀርቧል ወይም ኮሚሽኑን ማነጋገር ይሆናል።
በቪክቶሪያ እኩልነት መብት አስጠባቂና በሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አድራሻ፡ 3/380 Lonsdale St, Melbourne, Victoria, 3000 ፈቃድ የወጣ የታተመ ጽሁፍ ነው።

April 2007